የተማሪው ፎቶ
ከተለጠፈ በኋላ
የወረዳ ት/ት ጽ/ቤት
ማህተም
ይደረግበታል፡፡

# የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት
# የተማሪዎችና የግቢ ደህንነት አጠባበቅ ስርዓት
# በተማሪዎች፣ በወላጆችና በዩኒቨርሲቲ መካከል የሚገባ
# የኃላፊነት መውሰጃ ውል

## 1. መግቢያ

ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የተማሪዎችን ሁለንተናዊ እድገት በማጎልበትና በማጠናከር ወጣቶች ለራሳቸው፣ ለቤተሰቦቻቸው፣ ለኅብረተሰባቸውና ለሀገራቸው ማደግ፣ መሻሻልና መለወጥ ያላቸው ሚና ከፍተኛ ነው። ተቋማቱ ሀገር በዓለም ደረጃ ተወዳዳሪ ሆና እንድትወጣ ያላቸው አስተዋጽኦም በምንም የሚተካ አይደለም። ስለሆነም ተማሪዎች በእውቀት፣ በቴክኖሎጂ፣ በሳይንስና በምርምር የጎለበቱ፣ የለሙ፣ የላቁና የበቁ ሆነው የድህነት ቀንበር የከበዳት ሀገራቸውን የችግሯ መፍትሔ እንዲሆኗት ይጠበቃል። ሀገራቸውም ነገ ለችግሬ ደራሽ ይሆኑኛል በማለት ተንከባክባ የምታስተምራቸው በመልካም ዜግነታቸው ለማህበረሰባቸው ልዕልና ብርቱ ምሰሶ በመሆን ኩራትና ብርሃን እንጂ የችግርና የሃዘን ምንጭ ሊሆኑ አይገባም፤ አይጠበቅባቸውምም። ይሁንና ባለፉት ጥቂት ዓመታት በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተማሪዎች ባለማስተዋልና በስሜታዊነት እየተገፋፉ ራሳቸውን ለችግር ሲያጋልጡ፣ ቤተሰቦቻቸውን ደግሞ ለሃዘንና ለልብ ስብራት ሲዳርጉ እንዲሁም በተቋማቱ ንብረቶች ላይ ጉዳት ሲያደርሱ ተስተውሏል። ችግሮች ቢኖሩ እንኳ በሰላማዊ መንገድ በመግባባትና በመወያየት መፍታት የሚቻልበት ዕድል ሰፊ ሆኖ እያለ ተገቢ ባልሆነና ባልሰለጠነ ሁኔታ ሁከት፣ ጥፋትና ቀውስ መፍጠር በምንም ሁኔታ ተቀባይነት የለውም። በመሆኑም ሁሉም ተማሪዎች የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ያወጧቸውንም ሆነ የሚያወጧቸውን ደንቦችና ሕጎች አክብሮ መማር ግዴታቸው ሲሆን ጥያቄዎች የሚኖሩ ከሆነም በሰለጠነ መንገድ ለሚመለከተው የዩኒቨርሲቲ አመራር በማቅረብ ምላሽ ማግኘት ይቻላል። ተማሪዎች በተቋማቱ ቆይታቸው መብታቸው ተጠብቆ እንዲማሩ፣ ግዴታቸውንም እንዲወጡ ይደረጋል። ለዚህ ዩኒቨርሲቲውም ሙሉን ኃላፊንቱንና ተጠያቂነቱን የሚወስድ ይሆናል። ነገር ግን ኃላፊነታቸውን ሳይወጡ በዩኒቨርሲቲ ውስጥ ለሚያደርሱት ችግርም ሆነ ጥፋት ራሳቸውም ሆኑ ወላጆቻቸው ወይም አሳዳጊዎቻቸው ሃላፊነት መውሰድ ግዴታቸው በመሆኑ ውል የሚገቡበት ሰነድ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል።

## 2. ዓላማ

ይህ ውል የተዘጋጀው የተማሪዎችንና የተቋማቱን ሰላምና ደህንነት በማስጠበቅ ተማሪዎች ተረጋግተው በመማር የሚጠበቅባቸው ደረጃ ላይ እንዲደርሱ፣ መብታቸው ተጠብቆ ግዴታቸውን እንዲወጡ፣ ዩኒቨርሲቲውም ሙሉ ኃላፊነቱንና ተጠያቂነቱን እንዲወስድ ለማድረግና ተማሪዎችም ለሚያጠፉት ጥፋትም ሆነ ለሚያደርሱት ጉዳት እነርሱም ሆኑ ወላጆቻቸው ወይም አሳዳጊዎቻቸው ተጠያቂ መሆናቸውን ለማስገንዘብና ኃላፊነት እንዲወስዱ ለማድረግ ነው።

## 3. መመሪያ

ከዚህ ቀጥሎ ለቀረቡት ጥያቄዎች በተሰጡት ባዶ ቦታዎች በትክክል መረጃው ተሞልቶ ሰነዱ በወረዳው ትምህርት ጽሕፈት ቤት ኃላፊ ተረጋግጦና ማህተም ተደርጎበት በተማሪው እጅ ለዩኒቨርሲቲው ይላካል። የተሰጡት መረጃዎች ትክክለኛ አለመሆናቸውን ከተረጋገጠ ዩኒቨርሲቲው ተማሪውን ያሰናብታል።

## 4. መረጃዎች

### ሀ. በተማሪዎች የሚሞላ

i. የተማሪው ስም ______________ የአባት ስም ______________ የአያት ስም ______________
ጾታ ________ እድሜ ________

ii. የተመደበበት/የሚማረው የትምህርት መስክ
ሀ. ለአንደኛ ዓመት ተማሪዎች ☐ ማህበራዊ ሳይንስ ☐ ተፈጥሮ ሳይንስ
የዩኒቨርሲቲ መግቢያ ፈተና ውጤት ________ የተመደበበት ዩኒቨርሲቲ ______________

ለ. ሁለተኛ ዓመትና ከዚያ በላይ ተማሪዎች፡ የሚማርበት ዩኒቨርሲቲ ______________
የትምህርት ክፍል ______________ የትምህርት አመት ________

iii. አድራሻ፡ ክልል/ከተማ አስተዳደር______________ ዞን/ክፍለ ከተማ ______________ ወረዳ________
ቀበሌ ______________ የቤት ቁጥር ________ የተማረበት መሰናዶ ት/ቤት ______________
የተማሪው የሞባል ስልክ ቁጥር ______________ ሌላ ተጨማሪ የሞባይል ቁጥር (ካለ) ______________
የተማሪው አባት ስም ከነአያት ______________
የተማሪው እናት ስም ከነአያት ______________

እኔ ተማሪ ______________ በተመደብኩበት/በምማርበት ዩኒቨርሲቲ ተቋሙ ባሉት ሕግ፣ ደንብና መመሪያ ለመተዳደር፣ በሰላማዊ መንገድ ትምህርቴን ለመማርና ከሌሎች የዩኒቨርሲቲው ተማሪዎች ጋር በጋራና በአንድነት ተግባብቼ ለመኖር፣ በዩኒቨርሲቲው ሀብትና ንብረት ላይ ችግር እንዳይፈጠር በምችለው ሁሉ የበኩሌን ለመወጣት፣ ችግሮች ሲከሰቱ ለሚመለከተው አካል መረጃ ለመስጠትና የራሴንና የግቢውን ደህንነት ለመጠበቅ ቃል እየገባሁ፣ ችግሮች ሲገጥሙ ለሚመለከተው አካል በበሰለ አግባብ በማቅረብ መፍትሔ የምሻና በምንም ሁከትና አመጽ የማልሳተፍ መሆኑን ሳረጋግጥ ይህ ሳይሆን ቀርቶ ለሚፈጠረው ችግር ሕጋዊ እርምጃ ዩኒቨርሲቲው ሊወስድ የሚችል መሆኑን በመረዳት ለሚጠፋው ሁሉ በኃላፊነት የምጠየቅ መሆኔን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ።

የተማሪው ስም______________ ፊርማ ______________ ቀን ______________

## ለ. በወላጅ ወይም በአሳዳጊ የሚሞላ

i. የተማሪው ወላጅ ወይም አሳዳጊ ስም ከነአያት ______________________________ ጾታ ________ እድሜ ____________

ii. የወላጅ/አሳዳጊ አድራሻ፡ ክልል/ከተማ አስተዳደር______________________________ ዞን/ክፍለ ከተማ ______________________________

ወረዳ____________________ቀበሌ ____________________________ የቤት ቁጥር ______________

የሞባል ስልክ ቁጥር ______________________________ ሌላ ተጨማሪ የሞባይል ቁጥር (ካለ) ______________________________

እኔ ______________________________የተማሪ______________________________ ወላጅ(አሳዳጊ) በመሆን ልጄ በዩኒቨርሲቲ ቆይታው መልካም ስብዕና ኖሮት ሕግና ደንብን በማክበር እንዲማር፣ በዩኒቨርሲቲ ውስጥ በማንኛውም መነሻ በሚፈጠሩ ግጭቶችና ጥፋቶች በግልም ይሁን በቡድን እንዳይሳተፍ፣ ተባባሪም እንዳይሆንና በዩኒቨርሲቲው የተማሪዎች የዲስፕሊን መመሪያም ሆነ በሌሎች አካዳሚያዊና አስተዳደራዊ ሕጎችና ደንቦች ተገዢ እንዲሆን የመከርኩ ሲሆን፤ ነገር ግን ከዚህ በመውጣት ልጁ በጥፋቶች ተሳታፊና ተባባሪ በመሆን ለሚያደርሰው ጥፋትና ጉዳት ለሚወሰድበት እርምጃ በህግ ተጠያቂ እንደሆነ ያስገነዘብኩ መሆኑን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

የወላጅ ወይም ያሳዳጊ ሙሉ ስም ______________________________ ፊርማ __________________ቀን __________

## ሐ. በወረዳ ትምህርት ጽ/ቤት የሚሞላ

i. የወረዳው ትምህርት ጽሕፈት ቤት ኃላፊ ስም ከነአያት ______________________________

ii. የትምህርት ጽሕፈት ቤቱ አድራሻ፡ ክልል/ከተማ አስተዳደር______________________________ ዞን/ክፍለ ከተማ ______________________________

ወረዳ______________________________

የቢሮ ስልክ ቁጥር (ካለ) ________________ የፖስታ ሳጥን ቁጥር ______________________________

የጽሕፈት ቤቱ ኃላፊ የሞባይል ስልክ ቁጥር ______________________________ ሌላ ተጨማሪ የሞባይል ቁጥር (ካለ) ______________________________

እኔ በክልል/ከተማ አስተዳደር__________________________ በዞን/ክፍለ ከተማ__________________________ የ______________________ ወረዳ ትምህርት ጽ/ቤት ኃላፊ፣ የተማሪ______________________________ወላጅ ወይም አሳዳጊ ______________________________ የዚህን ውል ዓላማና የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎችን የዲስፕሊን መመሪያ እንዲሁም ተማሪዎች ማናቸውንም የዩኒቨርሲቲውን ሕጎችና ደንቦች በማክበር መንቀሳቀስ ግዴታ መሆኑን፣ መልካም ዜጋ በመሆን ሰላሙንና ደህንነቱን ማስጠበቅ እንደሚገባው ወላጆቹ /አሳዳጊዎቹ/ በተገኙበት ማብራሪያ የሰጠሁ መሆኔንና በዩኒቨርሲቲ ቆይታው በማንኛውም ምክንያት በግልም ይሁን በቡድን በሚፈጠሩ ግጭቶችና ጥፋቶች ተሳታፊ ወይም ተባባሪ እንዳይሆን ስልጠና የወሰደ ሲሆን ይህንን ተላልፎ ችግር ቢፈጥር ለሚደርሰው ጥፋት ሁሉ እሱም ሆነ ወላጆቹ/አሳዳጊዎቹ ተጠያቂ እንደሚሆኑ ያስገነዘብኩና በዚህ ሰነድ ላይ የተሰጡት መረጃዎችም በሙሉ ትክክለኛ መሆናቸውን አረጋግጣለሁ፡፡

የወረዳው ትምህርት ጽ/ቤት ኃላፊ ስም______________________________ፊርማ ______________________ቀን __________

(የጽ/ቤቱ ክብ ማህተም)

## መ. በዩኒቨርሲቲ ኃላፊ (ተወካይ) የሚሞላ

i. የዩኒቨርሲቲው ስም ______________________________

ii. የዩኒቨርሲቲው ተወካይ (የትምህርት ክፍል ኃላፊ) ሙሉ ስም ______________________________

ዩኒቨርሲቲው በአመቱ የትምህርት ዘመን መጀመሪያ ተማሪዎቻችን ሊመሩባቸውና ሊከተሏቸው የሚገቡ አካደሚያዊና አስተዳደራዊ ሕጎች፣ መመሪያዎችና ደንቦች በማስተዋወቅ፣ በቆይታቸው መልካም ስብዕና እንዲኖራቸው፣ በሙያ መስመራቸው የሚጠበቅባቸውን እውቀትና ክህሎት እንዲጨብጡ በማስረዳት፣ የተማሪዎቻችንን ሰላምና ደህንነት ለመጠበቅና በትምህርት ክፍሉ በሚሰጡ ትምህርቶች መምህራን በግልም ይሁን በቡድን የተማሪዎቻችንን መብት ለማክበርና ለማስከበር፣ ግዴታቸውን እንዲወጡ ለማስቻል የእውቀት አባትነትና ሙያዊ ኃላፊነት ያለብን መሆኑን በማስረዳት ውጤታማ ሥራ ለመሥራትና ለሁሉም ተማሪዎቻችን ያለአድልኦ ለማገልገልና ይህንም ተማሪ በሚቻለው ሁሉ በማገዝ አደራዬን እንደምወጣ ዩኒቨርሲቲውን ወክዬ በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

የዩኒቨርሲቲው ኃላፊ (ተወካይ) ስም______________________________ ፊርማ ________________

ቀን______________________________ (የዩኒቨርሲቲው ክብ ማህተም)

**ማሳሰቢያ፡-**

1. ተማሪው ወደ ተመደበበት ዩኒቨርሲቲ ሲሄድ በሁሉም በሚመለከታቸው አካላት የተፈረመበትንና የወረዳው ት/ጽ/ቤት ክብ ማህተም ያረፈበትን የዚህን ውል ፎርም ኦርጂናል ቅጂ ካላቀረበ መመዝገብ አይችልም፡፡
2. ይህ ውል በሶስት ቅጂዎች የሚፈረም ሲሆን አንዱ በተማሪው እጅ፣ ሁለተኛው በወረዳው ትምህርት ጽ/ቤት እጅ፣ ሶስተኛው በዩኒቨርሲቲው ሬጅስትራር ገቢ ሆኖ ከተማሪው ፋይል ጋር ይያያዛል፡፡
3. በዚህ ውል በወንድ ጾታ የተገለጸው የሴትንም ያጠቃልላል፡፡